# ትንታግ ፣ መድሀኒቱ

በሆድ የተገዛ ፣ ሹምባሽ አድር ባዩ
በህዝብ ያላገጠ ፣ ቅጥረኛ ሰላዩ
የባዕዳን ሎሌ ፣ አገር አስገንጣዩ
ቀኑ ተቃረበ ፣ አጠረ ገመዱ
ብርክ ያዘው ወያኔ ፣ ተሸበረ ሆዱ
ጨርቄን ፣ ማቄን አለ ፣ በዛ መርበድበዱ
ያ ! የቀድሞ መልኩ ፣ ታየ ፣ ወጣ አመዱ
ዛሬ ሳይሞት ሞቶ ፣ እንደዚህ መራዱ
መልዕክቱን ፣ ቢያገኝ ነው ፣ ከያውራ መንገዱ
ትንታጉ መጣበት ፣ ተማሰ ጉድጓዱ ።

ምዕራፉ ሊዘጋ ፣ ጊዜው ተቃረበ
ቀኑ ድንገት መሸ ፣ ባንዳ አኮበኮበ
እንዳበደ ውሻ ፣ ባዝኖ ተካለበ
መሹለኪያ ፣ ማምለጫው ፣ ሁሉም ተጣበበ
የወያኔ ጀሌ ፣ ሱሪው እረጠበ
በፍርሃት ራደ ፣ በላቡ ታጠበ ።

ምላሱ ታሰረ ፣ ተዘጋ አንደበቱ
መላወስ አቃተው ፣ ብርክ ያዘው ጉልበቱ
ክንዶቹም ታጠፉ ፣ ጠወለገ ፊቱ
ወያኔም ጀሌውም ፣ ገባ ከማጀቱ
ቀሚስ አጠለቀ ፣ ተሻምቶ ከሚስቱ
ዘጠኝ ጊዜ ሞተ ፣ እያለ በህይወቱ
ልቡ ከድታው ሄደች ፣ ላይቀርለት ሞቱ
የመቃብር አፎች ፣ ሁሉም ተከፈቱ
ቀኑ ተቃረበ ፣ ግብአተ መሬቱ
ጎራዴው ተስሎ ፣ ወጥቷል ከአፎቱ
ተመመ መጣበት ፣ ትንታግ መድሀኒቱ ።

ታዛቢው ... September 09, 2010